*4127 Redwood Road*
*Oakland, CA 94610*
*Tel: (510) 530 - 3681*

*ቀን/ Date _01-21-2007*
*ቁጥር/ Number____*

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ፩ አምላክ አሜን።

በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ
የሚመራው በስደት ሀገር የሚገኘው ሕጋዊው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክር
ስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ፥አዲስ የሾማቸውን ጳጳሳት አስመልክቶ፥ከዚህ ቀጥሎ በተዘረዘሩ
ት ነጥቦች ላይ መግለጫ አውጥቷል።

1. ዓለም አቀፋን የቤተ ክርስቲያን ቀኖና ያፈረሰው አካልና ያፈረሰበት ምክንያ
ት፤
2. የቅዱስ ፓትርያርኩና የብፁዓን አባቶች ሊቃነ ጳጳሳት መገፋትና መሰደድ፤
3. በስደት ሀገር የምትገኘው ቤተ ክርስቲያን እድገትና የአገልግሎት ስፋት፤
4. የጳጳሳቱ ሢመት እስካሁን የዘገየበት ምክንያት፤
5. የጳጳሳቱ ሢመት አሁን ያስፈለገበት ምክንያት፤
6. ማጠቃለያ መልእክት፤

<u>1. ዓለም አቀፋን የቤተ ክርስቲያን ቀኖና ያፈረሰው አካልና ያፈረሰበት ምክንያት፤</u>

ጥንታዊት፥ሐዋርያዊትና ታሪካዊት የሆነችው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስ
ቲያን ከተመሠረተችበት ጊዜ አንሥቶ በተለያዩ ዘመናት ፈተና ተለይቷት አያውቅም።

በእነዚህ ረጅም የታሪክ ዓረፍተ ዘመናት ሁሉ፥ብዙ ውድ የሆነ የሰው ሕይወት ጠፍቶባ
ታል፤ ብዙ የታሪክ ቅርስ ውድመት ደርሶባታል።

ይሁን እንጅ፥የመሠረታት ኢየሱስ ክርስቶስ ኃያል አምላክ በመሆኑ፥ኃዘንን አሳልፎ ደስ
ታን መስጠት ልማዱ ነውና፥ችግሩንና ፈተናውን ሁሉ አሳልፎ፥በድል አድራጊነት፥ ከዚህ
አሁን ካለንበት ዘመን አድርሷታል።
«በብዙ መከራ ተፈትነው ሳሉ፥የደስታቸው ብዛትና፥የድህነታቸው ጥልቅነት የልግስናቸው
ን ባለጠግነት አብዝቶአል ተብሎ እንደተጻፈ»። 2ኛ ቆሮ 8፥2

ቤተ ክርስቲያናችን ባሳለፈቻቸው ዘመናት ሁሉ የደረሰባት ችግር፥አሁን በዘረኛው የወያ
ኔ ኢሀዲግ አስተዳደር ካደረሰባት ችግር ጋር ሲነጻጸር፥እጅግ የባሰና የከፋ፥እስካሁንም
ድረስ ገና ፈውስ ያልተገኘለት ቁስል መሆኑ ለሁሉም ግልጽ ነው።

ዘረኛው የወያኔ ኢሀዲግ አስተዳደር ችግሩን ያደረሰባት ከዚህ በታች ባጭሩ በተገለጠ
ው መልኩ ነበረ።

*ሀ. ኀሰኛው ወያኔ አዲስ አበባን እንደተቆጣጠረ፥የመጀመሪያ ተግባሩ፥ቤተ ክርስቲያንን ማፍረስ ነበር። በእቅዱም መሠረት፥ከብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ጋር አብሬ አልሠራም ከማለቱም በላይ፥አስታጥቆ ባስገባቸው ካህናት መሰል ካድሬዎቹ አማካኝነት ቅዱስ ፓትርያርኩ ከሥልጣን የሚወርዱበትን በሀሰት የተቀነባበረ ጽሑፍ አዘጋጅቶ፥ጳጳሳቱን በዚህ ጽሑፍ ላይ ፈርማቸሁ አውርዱ ብሎ አዘዘ።ጳጳሳቱም ከጥቂቶቹ በስተቀር፥ይህ ጽሑፍ የሀሰት ጽሑፍ ስለሆነ በዚህ ላይ እንፈርምም በማለት አቋማቸውን ገለጡ።*

*ለ. በመቀጠልም፥ፓትርያርኩን ካላወረዳችሁ ብሎ፥ጠቅላላውን የቤተ ክህነቱን በጀት በማን አለብኝነት አገደ።*
*በሽማግሌ ቢጠየቅም፥ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስን ከላወረዳቸሁ፥መቸም ቢሆን በጀቱ ሊለቀቅ እይችልም ብሎ፥በድጋሚ እገዳውን አጸና። በዚህ ጊዜ፥ከጳጳሳቱ ጀምሮ በጠቅላላው የቤተ ክህነቱ ሠራተኛ በሙሉ፥በረኃብ እንዲቀጣና ሲቸግረው ለወያኔ ተገዥ እንዲሆን በኀጠኛው ወያኔ ውሳኔ ተላለፈበት።*

*ሐ. ከዚያም፥የብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስን ስም በሀሰት የሚያጠፉ አስታጥቆ ያስገባቸውን ካድሬዎቹንና ልዩ፥ልዩ የሀሰት ሰዎችን በተናጠልም በቡድንም ከአደራጀና ከአስነሣ በኋላ፥የቅዱስ ፓትርያርኩን ስም በሀሰት የሚያጠፉ ካድሬዎቹ የሚያደርጉትን የተቃውሞ ሰልፍና የሚበትኑትን የሀሰት ወረቀት በራዲዮ፥በቴሌቪዥንና በጋዜጣ እንዲሰራጭ አደረገ።*

*መ. ቅዱስ ፓትርያርኩን የሚደግፉ ሰላማዊ ሰልፈኞችን በተነ፤ ሰልፉን የሚመሩትንም አሰረ፤እውነቱን ለማስረዳት የሚጻፉ ጽሑፎችንም በዜና ማሰራጫዎች እንዳይተላለፉ አገደ።*

*ሠ. በመጨረሻም ፥ሕጋዊው ቅዱስ ሲኖዶስ መንፈሳዊ ተግባሩን እንዳያከናውን ግፈኛው ወያኔ  በተለመደው ሕገ ወጥ አሠራሩ የቅዱስ ሲኖዶሱን ጽ/ቤት አሸገ።*

*ረ. በማናቸውም ረገድ መንፈሳዊ ሕይወት የጎደላቸውንና ወያኔ የዘረኝነት መንፈሱን ያሳደረባቸውን ጳጳሳት አደራጅቶ፥በሥራ ላይ የሚገኘውን ሕጋዊውን ቅዱስ ሲኖዶስ በማፍረስ፥መፈንቅለ ሲኖዶስ በማድረግ ሕገ ቤተ ክርስቲያንን ሻረ፤ ሕጋዊውን ፓትርያርክም ከመንበራቸው ብቻ ሳይሆን፥ከመንበረ ፓትርያርኩ ግቢም አባረረ። በሕገ ወጥነት የራሱን የፖለቲካ ካድሬዎቹን በሲኖዶስ ስም አደራጅቶ፥የካድሬዎች የሲኖዶስ ኮሚቴ አቋቋመ።*

*ይህ የወያኔ የፖለቲካ ካድሬ ሕገ ወጥ የሲኖዶስ ኮሚቴም፥ኀጠኛው ወያኔ ኢሀዲግ ከአሜሪካ ያመጣለትን እና መልምሎ ያቀረበለትን አባ ጳውሎስን በሀሰት አምስተኛ ፓትርያርክ ብሎ  በተቀደሰችው መንበር ላይ በማስቀመጥ፥ቤተ ክርስቲያንን በሃይማኖት ስም ክህደት የተመሳበት የዘር ፖለቲካ መሰበኪያ መድረክ በማድረግ፥ቅዱሱን የቤተ ክርስቲያን መንበር አረከሰ።*
*ሰ. «ይህች ሹመት በአንድ ዘመን፥በአንድ ሀገር፥ለሁለት ሰዎች ልትሆን አይገባም። ይህ በአንድ ሀገር ከተደረገ ግን አስቀድሞ ለተሾመው ትጽና ይላል። ስለታመመ ፓትርያርክ ግን፥አእምሮ ያጣ እንኳን ቢሆን፥ይድናል ብለው ተስፋ የሚያደርጉት ከሆነ ይጠብቁት። በኋላ የሚድን ከሆነ በሚያልፍ በሽታ ምክንያት፥ፍጹም ድኅነትን እስከሚያገኝ ድረስ ልትጸናለት ይገባልና። ከሹመት መሻር ግን ፍጹም ጉድለት ይገኝበታል። በተለያየ ደዌ ቢያዝ፥ ድኅነትን ተስፋ ስለሚያደርግ፥ሊጠብቁት ይገባል።ፍትሐ ነገሥት*

ፍትሐ መንፈሳዊ አንቀጽ 43፥4 /70 -78) የሚለውን ዓለም አቀፉን የቤተ ክርስቲያን ቀኖና በመጣስ ሕጋዊውን ፓትርያርክ በህመም ምክንያት ከመንበራቸው ብቻ ሳይሆን፥ ከመንበረ ፓትርያርኩ ግቢም አባረረ፤ በሀገራቸውም እንኳን እንዳይኖሩ በልዩ ልዩ ዛቻ ና ማስጠንቀቂያ በማስፈራራት ከቅድስት ሀገር ኢትዮጵያ አሳደዳቸው።

## 2ኛ. ቅዱስ ፓትርያርኩና ሊቃነ ጳጳሳቱ የተሰደዱበት ዋና ምክንያት፤

ሰው የሚወደውን ሀገሩን ጥሎ የሚሰደደው፥ሊሸከመውና ሊቋቋመው፥ከሚችለው ከአ ቅሙ በላይ የሆነ ችግር ሲያጋጥመው ብቻ ነው። ለልማዱ ሰው ሲበደል አቤት የሚ ለው ለመንግሥት ነበር። በዚህ ወቅት ግን በደሉን የሚፈጽመው፥ከበረሀ ወደ ከተማ የገባው፥የወያኔ ኢሀዲግ መንግሥት ስለሆነ፥ስሚ ዳኛ በመጥፋቱ፥ችግሩ ከአቅም በላይ ከባድ ስለነበረ፥ቅዱስ ፓትርያርኩን ጨምሮ፥ስድስት ሊቃነ ጳጳሳት፥ከሁሉም በላይ የሚወዷትን ሀገራቸውን ትተው፥ለመሰደድ ተገደዱ። የተሰደዱበት ምክንያትም የቤተ ክርስቲያን ክብር ተነካ፥ሕግ ተጣሰ፥ዓለም አቀፉ ቀኖና ቤተ ክርስቲያን ፈረሰ፤ ብለው ነው እንጅ፥የግል ክብራችን ተነካ ብለው አልነበረም። ወይም የግል ችግር ኑሮባቸው ም አይደለም።

## 3ኛ በስደት ሀገር የምትገኘው ቤተ ክርስቲያን እድገትና የአገልግሎት ስፋት፤

«ነገር ሁሉ ለበጎ ነው፤ተብሎ እንደተጻፈ፥ የዮሴፍ መሸጥ፥የሙሴ ስደት፥የእስጢፋኖስ ሞት፥ለበጎ እንደሆነ ሁሉ፥ የእነዚህን ሊቃነ ጳጳሳት ስደት፥እግዚአብሔር ባወቀ ለበጎ አደረገው። ስደታቸውንም እንደ ዮሴፍና እንደ ማኅበረ እስጢፋኖስም ባረከው።

የኢትዮጵያ ሕዝብ ካለፉት ሠላሳና አርባ ዓመታት ጀምሮ፥በልዩ ልዩ ምክንያት በዓለም ዙሪያ ተበትኗል።የጠፉትን እንዲፈልግ፥ የተበተኑትን እንዲሰበስብ፥አንድያ ልጁን ወደ ዓለም የላከ፥የእሥራኤል ዘነፍስ እውነተኛ እረኛ፥እግዚአብሔር፥አሁንም ሕዝቡ በዓለ ም በረሃ ተውጦና ባዝኖ እንዳይቀር ስለፈለገ፥እነዚህን አባቶች መንጋውን ይሰበስቡለት ዘንድ በማይመረመር ጥበቡ በስደት ምክንያት ከሀገር አወጣቸው።

እነዚህ አባቶች፥በስደት ሀገር ያለውን ሕዝብ ለማሰባሰብ፥ከዚህ እንደሚከተለው ተንቀሳ ቅሰዋል።

ሀ. በሕጋዊው ፓትርያርክ የሚመራው፥ሕጋዊው ቅዱስ ሲኖዶስ ለመጀመሪያ ጊ ዜ በስደት ሀገር፥በኒውዮርክ ከተማ መስከረም 20 ቀን 1987 ዓ/ም ባደረገው ስብሰባ፥ ሥራውን ይፋ አድርጓል። ጠቃሚ ውሳኔዎችንም አስተላልፏል። ከዚህ በኋላ፥ብፁዓን አበው ሊቃነ ጳጳሳት በቅዱስ ሲኖዶስ ውሳኔ መሠረት፥በየቦታው እየተዘዋወሩ በማስተ ማርና በመባረክ፥አዳዲስ አብያተ ክርስቲያናትንም እንዲታነጹ በማድረግ ከፍተኛ አገ ልግሎት አበርክተዋል። ለዚህም የታነጹት አብያተ ክርስቲያናትና ተገልጋዮቹ ምእመና ን በቂ ማስረጃዎች ናቸው።

ለ. አገልጋይ ካህናትን በብዙ ጥረት፥ከሀገር ቤት በማስመጣት ያለ ዕረፍት፥ከክ ፍለ ሀገር፥ወደ ክፍለ ሀገር፥ከአህጉር ወደ አህጉር በመዘዋወር፥በሚሰጡት አገልግሎት እነሆ በስደት ሀገር ያለችው ቤተ ክርስቲያን አሁን ካለችበት ከፍተኛ የእድገት ደረጃ ልትደርስ ችላለች።

## 4ኛ. የጳጳሳቱ ሢመት እስካሁን የዘገየበት ምክንያት፣

በስደት ሀገር ለምትገኘው ቤተ ክርስቲያን፥የተሟላ አገልግሎት ለመስጠት፥በሕጋዊው ፓትርያርክ የሚመራው ሕጋዊው ቅዱስ ሲኖዶስ፥ጳጳሳትን መሾም እንደሚገባ ተስማም ቶ ካመነበትና ከተወሰነ፥ስምንት ዓመት ሁኖታል። ተግባራዊነቱ የዘገየበት ምክንያት ግን፣

ሀ. የእግዚአብሔር ቅዱስ ፈቃዱ እንዲሆን እየጸለየበት፣

ለ. በሕግ አፍራሹ በአባ ጳውሎስ የሚመራው፥ሕገ ወጡ ሲኖዶስ፥ከዛሬ ነገ፥ ስህተቱን ያርማል፥የጣሰውንም ሕግ ያስተካክል ይሆናል በማለት፤

ሐ. አሳዳጁ መንግሥትም፥ከዛሬ ነገ፥ይሰክን ይሆናል፥በቤተ ክርስቲያኒቱ ላይ የፈጸመው በደል ተሰምቶት የጫነባትን ከባድ የብረት ቀንበር፥ያቀልል ይሆናል፤ ቤተ ክርስቲያኒቱም ከስደት ትመለስ ይሆናል በማለትና እርቆ በማሰብ ነበር።

ነገር ግን አሳዳጁ መንግሥትም ሆነ ሕገ ወጡ አባ ጳውሎስ፥በቃልም ሆነ በተግባር፥ ምንም ዓይነት የሰላም ምልክት አልታየባቸውም። እንዲያውም በስደት የሚገኙትን የአባቶችን ሊቃነ ጳጳሳት ስም፥ለሌሎች በህገ ወጥነት ለመለመሏቸው ካድሬዎቻቸው በመስጠትና የሀገሪቱንም ሆነ የቤተ ክርስቲያንን ህልውና ለፈተና እና ለከባድ ችግር የጣሏት የነገን የሚያሰቡ፥ይሉኝታ የሌላቸው ከሀዲዎች መሆናቸውን ከሚያከናውኗቸ ው የክህደት ተግባሮች፥ከሚያስተላልፏቸው መልእክቶችና ጋዜጣዊ መግለጫዎች ለማ ወቅ ተችሏል።

<u>«ቢሆንም ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር የለምና፥በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ የሚመራው ሕጋዊው ቅዱስ ሲኖደስ፥ የሀገሪቱም ሆነ፥የቤተ ክርስቲያኒቱ ችግር የሚወገድበትን፥ብሔራዊ እርቅ የሚመጣበት ን፥የተሰደዱት የሚመለሱበትን፥የታሰሩት የሚፈቱበትን፥በሀገራችን ሰላምና መልካም አ ስተዳደር የሚሰፍንበትን ጊዜ፥እግዚአብሔር እንዲያፋጥነው፥ዘወትር እየጸለየ፥የሰላም ኮሚቴ አቋቁሞ፥በሩን ለሰላም ክፍት አድርጎና ዝግጁ ሆኖ በናፍቆት ይጠብቃል።</u>

## 5ኛ የጳጳሳቱ ሢመት ያስፈለገበት ምክንያት፤

ሀ. በስደት ሀገር ያለችውን ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ደከመን፥ሰለቸን፥ሳይሉ ያለ ዕረፍት የሚያገለግሏት ብፁዓን አበው ሊቃነ ጳጳሳት፥በቍጥር ጥቂቶች ስለሆኑ፤

ለ. ብፁዓን አበው ሊቃነ ጳጳሳት፥እግዚአብሔር ጸጋውን ያበዛላቸው፥ቢሆኑም፥ በዕድሜ የገፉ፥አረጋውያን ስለሆኑ፥በጀመሩት መንፈሳዊ የክህነት አገልግሎት፥በእግራቸ ው ተተክተው፥ቤተ ክርስቲያንን የሚመሩ፥አባቶችን መሾም ተገቢ ስለሆነ።

ሐ. ከአባቶቻችን ከሐዋርያት ጀምሮ፥ቀኖና ቤተ ክርስቲያን በሚያዝዘው በሕጋዊ መንገድ፥ሰንሰለቱንና መሥመሩን ጠብቆ፥እስከ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ ፓትር ያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ የመጣውን፥ሀብተ ክህነት፥በሕጋዊ መንገድ ለት ውልድ ማስተላለፍ ተገቢ ስለሆነ ነው።

*በጠቅላላውም፥በውጭ ሀገር፥በስደት የምትገኘው ቤተ ክርስቲያን፥እየሰፋችና እያደገች ስለመጣች፥በአሁኑ ወቅት የተከናወነው የጳጳሳት ሢመት፥ሕጋዊም፥ወቅታዊም፥አስፈላጊ ም፥ተገቢም ስለ ሆነና፥የእግዚአብሔር ቅዱስ ፈቃዱ፥የሚፈጸምበት ጊዜም ስለ ደረሰ ነው።*

*«እናንተ ገና አራት ወር ቀርቷል፤መከርም ይመጣል ትሉ የለምን? እነሆ እላችኋለሁ፤ ዓይናችሁን አንሡ። አዝመራውም አሁን እንደነጣ፤ እርሻውን ተመልከቱ»። ተብሎ እንደተጻፈ።* *ዮሐ 4፥35*

*ዳግመኛም፥-ወይቤሎሙ ለአርዳኢሁ፥«ማእረሩሰ ብዙኅ፥ወገባሩ ኅዳጥ፥ሰአልዎ እንከ ለበዐለ ማእረር፥ከመ ይወስክ፥ገባረ ለማእረሩ።» ደቀ መዛሙርቱንም እንዲህ አላቸው፤ መከሩ ብዙ ነው፤ ሠራተኛው ግን ጥቂት ነው፤ስለመከሩ ሠራተኛ ይጨምር ዘንድ የመከ ሩን ባለቤት ለምኑት፥ተብሎ እንደተጻፈ።* *ማቴ 9፥37*

## *<u>6ኛ. ማጠቃለያ መልእክት፤</u>*

*በሰሜን አሜሪካና በአውሮፓ፥በአፍሪካና በአውስትራልያ፤እንዲሁም በመላው ዓለም የምትገኙ፥የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ፥ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ምእመናን ሆይ !*

*የጌታችን፥የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋና ሰላም ይብዛላችሁ።*

*እነዚህ በዛሬው ዕለት የተሾሙት ጳጳሳት፥የተሾሙት፥ለምቾትና ለድልወት አይደለም። በስደት ሀገር ምቾትና ድልወት የለምና። በኢትዮጵያ ይደረግ እንደነበረው፥በታወቀ በ ጀት፥በተሠራ ቤት፥እየተንደላቀቁ ሊኖሩ፥ወይም እንደ ባለሥልጣን ሊመሩ አይደለም።*

*ነገር ግን በስደት ሀገር የሚደርስባችሁን ችግራችሁንም ደስታችሁንም፥እየተካፈሉ፥ ራሳቸውን ዝቅ አድርገው፥በትሕትና ሊያገለግሏችሁ ነው እንጅ።*

*የአሕዛብ አለቆች እንዲገዙአቸው፤ታላላቆቹም በላያቸው እንዲሠለጥኑ፥ታውቃላችሁ። በእናንተስ እንዲህ አይደለም፤ ነገር ግን፥ማንም ከእናንተ ታላቅ ሊሆን የሚወድ፥የእና ንተ አገልጋይ ይሁን፤ከእናንተም፥ማንም ፊተኛ ሊሆን የሚወድ፥የእናንተ ባሪያ ይሁን። እንዲሁም የሰው ልጅ፥ሊያገለግል፥ነፍሱንም ለብዙዎች ቤዛ ሊሰጥ እንጅ፥እንዲያገለግ ሉት አልመጣም። ተብሎ እንደተጻፈ»።* *ማቴ 20፥25*

*ስለዚህ በመልካም እንድትቀበሏቸው፥ቃላቸውንም እንድትሰሟቸው፥በመንፈሳዊ የክህነ ት አገልግሎታቸውም እንድትጠቀሙ ቅዱስ ሲኖዶስ በጌታችን፥በመድኃኒታችን በኢየ ሱስ ክርስቶስ ስም አደራ ይላል።*

*«እናንተን የሚቀበል እኔን ይቀበላል፤ እኔንም የሚቀበል የላከኝን ይቀበላል።ተብሏልና። ማቴ 10፥40»*

*ዳግመኛም «ወዘኪያክሙ ሰምዐ፤ኪያየ ሰምዐ፤ ወዘለክሙ አበየ ሊተ አበየ፤ ወዘ ሊተ አበየ አበዮ፥ለዘፈነወኒ፤ ወዘኪያየ ሰምዐ፥ሰምዖ ለዘፈነወኒ።»*

«እናንተን የሰማ፥እኔን ሰማ፤ እናንተን እምቢ ያለ፣እኔን እምቢ አለ። እኔንም እምቢ ያለ የለከኝን እምቢ አለ፤ እኔንም የሰማ፥የላከኝን ሰማ። እንዳለ መድኃኒታችን በወንጌ ለ መንግሥቱ።»                ሉቃ 10፥16

«ዳግመኛም ተአዘዙ ለመኳንንቲክሙ፥ወተኰነኑ ሎሙ፤እስመ እሙንቱ ይተግሁ በእን ተ ነፍስክሙ፤ ከመ ዘይትሐሰብዎሙ በቅድመ እግዚአብሔር በእንቲአክሙ ከመ በፍ ሥሐ ይግበርዎ ለዝንቱ ወኢይንሐኩ።»

ለመምህሮቻችሁ ታዘዙ፣ተገዙላቸውም፤እነርሱ ስለ ነፍሳችሁ ያሥባሉና፣በእግዚአብሔ ር ፊት ስለ እናንተ የሚተሣሰቡአቸው እንደመሆናቸው መጠን፣ይህን ደስ ብሎአቸው ያደርጉት ዘንድ፥ሳያዝኑ።» እንዳለ ሐዋርያ ጳውሎስ፤                ዕብ 13፥17

የተወደዳችሁ ምእመናን ! የጌታችን የመድኃኒታችን፥የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋና ሰላም ይብዛላችሁ። የቅዱሳን አባቶቻችን የሐዋርያት በረከት ይደርባችሁ።

ሰላም ለሀገራችን ለኢትዮጵያ ይሁን፤
ሰላም ላለንባት ሀገር ለአሜሪካ፤
ሰላም ለመላው ዓለም ይሁን።

«እንግዲህ በእኛ እንደሚሠራው፥ኃይል መጠን፥ከምንለምነው ወይም ከምናስበው ሁሉ ይልቅ፥እጅግ አብልጦ ሊያደርግ ለሚቻለው፥ለእርሱ በቤተ ክርስቲያን፥በክርስቶስ ኢየ ሱስ እስከ ትውልዶች ሁሉ፥ከዘላለም እስከ ዘላለም ክብር ይሁን አሜን!! ኤፌ 3፥20

ሕጋዊው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ ጽ/ቤት፤

ዋሽንግተን ዲሲ፤

ጥር ፲፫ ቀን ፲፱፻፺፱ ዓ/ም        **(January 21, 2007)**